የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail:-info@ethionet.et

ቁጥር
Ref. No. ____________
ቀን
Date ____________

ሚያዚያ 25 ቀን 2003 ዓ.ም

<u>ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ የተሰጠ መግለጫ</u>

# የአባይ ወንዝ ግድብ ለእውነተኛ ብሔራዊ ጥቅም እንጂ ለፖለቲካ ኘሮፖጋንዳ መሆን የለበትም!

ሀገራችን ኢተዮጵያ በተፈጥሮ የታደለች ሀገር ብትሆንም በመልካም አስተዳደር እጦትና ብሔራዊ ጥቅምን ለማስከበር ከሚደረግ ጥረት ማነስ... ከዛሬ 50 ዓመት በፊት ጀምሮ የተጠናው የአባይ ወንዝ ግድብ ለጐረቤት ሀገሮች ትልቅ የኢኮኖሚ አውታር ሆኖ ሲያገለግል ለባለቤቶቹ ግን ከዜማ እንጉርጉሮ የዘለለ ያተረፈልን ፋይዳ አልነበረም፡፡

ኢህአዴግ ሰሞኑን ታላቁ የሚሊኒየም ግድብ በማለት ድንገት ይዞት ብቅ ያለው ይህ አጀንዳ ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ህዝብ ሲመኘውና ሲጠብቀው የነበረ የረጅም ጊዜ ህልማችን ቢሆንም በአምስት አመቱ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሳይካተት ዛሬ በድንገት ያቀረበልን የምስራች በተግባራዊነቱ ላይ ትልቅ ጥርጣሬ እንዲኖረን አድርጓል፡፡

የአባይን ግድብ ለማጠናቀቅ ያስፈልጋል የተባለው የገንዘብ መጠን ከፍተኛ መሆንና የመንግሥት ቅድመ ዝግጅት አለመኖር፣ እንዲሁም በአምስት አመቱ የእድገትና የለውጥ ዕቅድ ውስጥ አለመካተቱ በሀገራችን የልማት ስኬት ላይ ጥያቄ ሊያስከትል የሚችል ከመሆኑም በላይ ዜጐች ለግድቡ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የተላለፈው ጥሪና አሁን በየመሥሪያ ቤቱ በማኔጅመንት ኮሜቴ እየተወሰነ የሚተላለፈው የእርዳታ መግለጫ የሠራተኛው ፍላጐት ስለመሆኑ አጠያያቂ ነው፡፡ በመሆኑም በአፈፃፀም ላይ የሚኖረውን ግልፀኝነትና ተጠያቂነት እንድንጠራጠር ያደርጋል፡፡

ኢህአዴግ በእየደረጃው በኃላፊነት ያስቀመጣቸው አመራሮች ኃላፊነታቸውንና ህዝባዊ አደራቸውን በአግባቡ ከመወጣት ይልቅ የግል ጥቅም በማሳደድ የሀገርና የህዝብን ንብረት ለግል ብልፅግና ሲያውሉ በሙስና ይፈለጋሉ የሚለው የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ያለፉት ተደጋጋሚ መግለጫዎች ለዛሬው ስጋታችን በር ከፋች ሆነው ይታያሉ፡፡ በያዝነው አመት እንኳ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ አንዳንድ ከተሞች ዘንድ የተደረገው የመሬት አስተዳደርና አያያዝ ችግር ሙስና በሀገራችን ምን ያህል ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን አሳይቶናል፡፡

የግብፅ የዲኘሎማሲ ቡድንም በሀገራችን ያለውን የህዳሴ ግድብ አስመልክቶ ከመንግሥት ባለስልጣናት ጋር ያደረገው ንግግር የሁለቱንም ሀገሮች ፍትሀዊ የህዝብ ጥቅም እንደሚያከብር መግለጹ በተፈጥሮ ሀብታችን የመጠቀም መብታችንን መገንዘባቸውን የሚያመለክት በመሆኑ በበጐ ጐኑ የሚታይ ነው፡፡

የአባይን ወንዝ ግድብ ለሀይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ብቻ ሳይሆን በምግብ ራሳችንን ለማስቻል የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ የመስኖ አገልግሎትም እንዲሰጥ ግድቡ ዕቅድ ሊታቀፍ እንደሚገባው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ያምናል፡፡

ለህዳሴው ግድብ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከዕለት ጉርሱ እየቀነሰ ለዚህ ታላቅ አላማ መሳካት እየከፈለ ያለው የገንዘብ መዋጮ ለተፈለገው ግብ እንዲውል እጅግ ጥንቃቄ ሊደረግበት እንደሚገባ እየገለጽን በአፈፃፀም ችግርና በኪራይ ሰብሳቢነት ዕቅዱ አልተሸፈነም የሚለው የተለመደው የገዢው ፓርቲ የፖለቲካ ጨዋታ ከወዲሁ እንዲገታ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/ ያሳስባል፡፡

## የኢትዮጵያ የህዝብ ትግል ያሸንፋል

## የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት /መኢአድ/

## ሚያዚያ 25 ቀን 2003 ዓ.ም

## አዲስ አበባ